ማርች 17፣ 2023

ውድ የ Montclair የአካዳሚክ እና ማበልፀጊያ ትምህርት ቤት ማኅበረሰብ፣

እስካሁን ድረስ ለርዕሰ መምህር ምርጫ ሂደቱ ስላበረከታችሁት ያልተቋረጠ ትብብር እናመሰግናችኋለን። በቅጥር ሂደቱ ቀጣይ ደረጃዎች ላይ የሚሳተፉ ሶስት እጩዎችን ያገኘን መሆኑን ስንገልጽላችሁ ደስ እያለን ነው።

- Adrienne Warner Lopez
- Daniel Barks
- Jessica Lujan
- Miranda Smith

የማህበረሰብ ተሳትፎ የDPS የርዕሰ መምህር ምርጫ ወሳኝ ክፍል በመሆኑ ማህበረሰባችንን የከፍተኛ እጩዎቻችንን ንግግር ከራሳቸው አንደበት እንዲሰማ ለማስቻል የቨርቹዋል የማህበረሰብ ገለጻ ሂደት አዘጋጅተናል። ይህ ሂደት የሚከተሉትን ይይዛል፦

- እጩዎች ለMontclair ያላቸውን ራዕይ እና በቀዳሚው የማህበረሰብ ግብዓት ዳሰሳ ጥናት እና የትምህርት ቤት ትብብር ኮሚቴዎች (CSC) አማካኝነት ለተጠየቋቸው ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽ አጭር ማጠቃለያ የያዘ በቅድሚያ የተቀረጸ ገለጻ ያስገባሉ። አመልካቾች ስለሚከተሉት እንዲናገሩ ተጠይቀዋል፦
    - እስኪ ስለ እራስዎ በጥቂቱ ይግለጹልን። ለ**Montclair Elementary** ምርጡ እጩ ነኝ ብለው የሚያስቡት ለምንድን ነው?
        - በ**Montclair** ውስጥ በቀጣዩ ዓመት እና ከዚያ በኋላ ስኬት ምን ሊመስል እንደሚችል በተመለከተ ራዕይዎ ምንድን ነው?
        - የተማሪዎቻችንን የማህበራዊ ስነ ልቡና ፍላጎቶች እንዴት በተጨማሪ ማሳካት እንችላለን?
        - ከቤተሰቦችና ማህበረሰቡ ጋር ተጨማሪ ግንኙነቶችን እንዴት ይመሰርታሉ?
- የእጩ ገለጻና የጥያቄ ምላሾች ከእጩው ግለ ታሪክ ጋር አብሮ በትምህርት ቤቱ ድረገጽ ላይ ይለጠፋሉ። የተቀረጹት ገለጻዎችና ግለ ታሪኮች በትምህርት ቤቱ ድረገጽ ላይ የማህበረሰብ አባላትን በበላይ ተቆጣጣሪው ለሚተላለፈው የመጨረሻው የቅጥር ውሳኔ መረጃ በመስጠት እንዲረዳን በእጩዎች ጥንካሬዎችና ታሳቢዎች ላይ ግብረ መልስ እንዲሰጡ ከምንጋብዝበት የዳሰሳ ጥናት ጋር አብሮ ይለጠፋል።

ለሁሉም ባለድርሻ አካላቶቻችን ድምጾች ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን። ይህን ለማስተናገድ እንዲያስችለን ሰራተኞችን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆችን እና የማህበረሰብ አባላትን የእጩዎችን ገለጻዎችና ግለ ታሪኮች በ፡ https://bit.ly/MontclairPrincipal2023 ገብተው እንዲያዩ እንጋብዛለን። እባክዎ ስለ እያንዳንዱ እጩ ጥንካሬዎች እና ታሳቢዎች የተመለከተ ግብረ መልስ በእጩዎቹ ገለጻዎችና የMontclair ፍላጎቶች ላይ ተመስርተው አስተያየት ይስጡ። ግብረ መልሱ በዳሰሳ ጥናቱ ወይም ለቤተሰብና ማህበረሰብ ተሳትፎ ቢሮ በስልክ ቁጥር 720-423-3054 በመደወል አስተያየት መስጠት ይቻላል። በተጨማሪም የግብረ መልስ ምላሾች በኢሜይል lori_nail@dpsk12.net ሊላኩ ይችላሉ። እባክዎ ሁሉንም ግብረ መልሶች እስከ ሰኞ፣ ኤፕሪል 3፣ 2023 በ 10 a.m. ሰዓት ድረስ ያጠናቁ።

የማህበረሰብ ግብረ መልስ ዳሰሳ ጥናት (እንግሊዘኛ/ስፓኒሽ)፦ https://bit.ly/MontclairFeedback-2023

የማህበረሰብ ግብአት መስጫ ወቅት ከተዘጋ በኋላ ግብረ መልሶቹ ለበላይ ተቆጣጣሪው የመጨረሻ የርዕሰ መምህር ምርጫ መረጃ በመስጠት እንዲረዱ ለማጋራት አንድ ላይ ይጠናቀራሉ። የመጨረሻዎቹ እጩዎች እንደ ቅጥር ሂደቱ የመጨረሻ ደረጃ በበላይ ተቆጣጣሪው የቅጥር ውሳኔ በDr. Alex Marrero፣ የትምህርት ቤቶች ምክትል ዋና ተቆጣጣሪው በDr. Tony Smith፣ በትምህርት ቤቶች ኃላፊ በCesar Cedillo እና በትምህርት ቤቶች ተባባሪ ኃላፊ በDrew
Coleman በሚካሄድ ቃለ መጠይቅ ላይ ይሳተፋሉ።

ስለ ተሳትፎዎ በድጋሚ እያመሰገንን የማህበረሰባችን ድምጾች መወከላቸውን የሚያረጋግጡልንን ዘዴዎች እንፈልጋለን።

ከሰላምታ ጋር፣

Dana Williams
የትብብር ዳይሬክተር፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 3

Scott Wolf
የክወና አገልግሎቶች ዳይሬክተር